# የቤተ ክርስቲያን ማሳሰቢያ

**የአርብ ፕሮግራም**

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች።

**የአገልግሎት ጥሪ**

በተለያየ መስክ ለማገልግለ የምትፈልጉ ሽማግሌዎችን አነጋግሩ።

**እርስ በርስ እንተያይ**

የጀምርነውን ለሌሎች ወገኖቻችን የመደወል እና እርስ-በእርስ የመጠያየቁን ነገር አጥብቀን እንድቀጥል ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። በዚህ አገልግሎት እየተጋችሁ ያላችሁ ወገኖች እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፤ 30-31)



- ⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
- ⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**

**773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)**
**773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)**
**630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)**
**773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)**
**773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)**

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10

# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!




"መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል።"
(ዮሐ. 10:11)

| Chicago Yemsrach Evangelical Church<br>4455 N. Seeley Avenue<br>Chicago, IL 60625 | መደበኛ ፕሮግራሞች<br>እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.<br>አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m. |
|---|---|
| **February 9, 2020** | **የካቲት 1፤ 2012 ዓ.ም.** |

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| **ጸሎት** ............................ | ወንድም መኮንን ጂኔሎ |
| **አምልኮ**.......................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| **ፕሮግራም መሪ** ............. | ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ |
| **ቃል** ............................... | ወ/ም ረድኤቱ ካሳ |
| **ማጠቃለያ** ..................... | ፕሮግራም መሪ |

## የሳምንቱ ጥቅስ

"ንብ ማርን እንዲከብብ ከበቡኝ፥ እሳትም በእሾህ ውስጥ እንዲነድድ ነደዱ፥ በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኋቸው።"
(መዝ. 118:12)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645 |
| ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሰኞ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ሲሳይ መሸሻ | | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ኮከቤ አስረስ | | |
| ወ/ም ዘሪሁን/ዮሐንስ | | |
| ወ/ም አያሌው/ጸደቀ | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

**እግዚአብሔር እረኛዬ ነው -- በትርህና ምርኲዝህ እነርሱ ያጸናኑኛል።**

ሰሞኑን በተከታታይ እያየን እንዳለነው እግዚአብሔር እረኛችን ነው -- ይመግበናል፤ እግዚአብሔር እረኛችን ነው -- ይመራናል፤ እንዲሁም ከኛ ጋር ያለው እግዚአብሔር የሞትን ኃይል ስለሻረው በሞት ጥላ መካከል ብናልፍ እንኳ ክፉን አንፈራም። ዛሬ ደግሞ እግዚአብሔር እረኛችን ጠባቂያችን እንደሆነ እንመለከታለን። የእግዚአብሔር እረኝነት ከሚገለጥበት አስደናቂ መንገድ አንዱ ጥበቃው ነው።

እውነተኛ እረኛ ለበጎቹ እራሱን ያኖራል። ጌታ ኢየሱስ ስለዚህ ጉዳይ ሲናገር "መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል። እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ ሞያተኛ ግን ተኵላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፤ ተኵላም ይነጥቃቸዋል በጎቹንም ይበትናቸዋል" (ዮሐ. 10:11-12) ብሏል። የእውነተኛ እረኛ ባህሪ በጎቹን ነፍሱን እስከ መስጠት ድረስ መውደዱ ነው። ስሊዚህ ጌታ ነፍሴን ስለ በጎቹ አኖራለሁ አለ። እውነተኛ እረኛ ስለበጎቹ ከጠላት ጋር ይገጥማል። ጠላት ሲነጥቃቸው ሲመጣ ተከትሎ ያስጥላቸዋል። ዳዊት ይህ የገባው እረኛ ስለሆነ አንበሳና ድብ መጥቶ በጎቹን ሲነጥቅ ተከታትሎ ይመታዋል፤ በጎቹንም የጠላቱን ጉሮሮ አንቆ ከአፉ ያስጥላቸዋል (1 ሳሙ. 17፡ 34-35)። እረኛችን ብርቱና ጽኑ ነው። አስተማማኝ ነው። ማንም ከእጁ ሊነጥቀን የሚችል የለም። ጌታችን ስለዚህ ጉዳይ ሲናገር "ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም" (ዮሐ. 6:37) በማለት አስተማማኝ ጥበቃውን አረጋግጦልናል።

ዳዊት እርሱ ለበጎቹ ትጉ እረኛ እንደሆነ እንዲሁ እግዚአብሔርም እርሱን የሚጠብቅ ትጉ እረኛ መሆኑን ተረድቶ ይዘምራል። ስለዚህም ዳዊት በእረኛው በትርና ምርኩዝ ይጽናናል። በትር እረኛው ጠላትን የሚመታበት ነው። በበትር ኃይል ይገለጣል። ሊያጠቃ፣ ሊነጥቅና ሊያጠፋ ጠላት ሲመጣ እረኛው አስተማማኝ በትሩን አንስቶ ጠላትን ይመታዋል። ቁም ነገሩ ጠላት አለመምጣቱ አይደለም። ጠላት ሊመጣ ይችላል። ጠላት ሊከብብ ይችላል። ነገር ግን "ንብ ማርን እንዲከብብ ከበቡኝ፥ እሳትም በእሾህ ውስጥ እንዲነድድ ነደዱ፥ በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኋቸው" (መዝ. 118:12) እንዳለ ዘማሪው ጠላት ቢከብብም እንኳ በአምላካችን የስሙ ኃይል ይቃጠላል፣ ይነዳል፣ ይበተናል። የጌታ ስም ጠላት የሚመታበት ብርቱ "በትር" ነው። ስለዚህ ከኛ ጋር ያለው ብርቱ ስለሆነ በጥበቃው እንታመናለን።

ዳዊት በእረኛው በትር ብቻ ሳይሆን በምርኩዙም ይታመናል። ምርኩዙ ከመስመር ስንወጣ የምንመለስበት፣ ስርዓት የምንይዝበት ነው። ቃሉ "እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል ለጥቅማችን ይቀጣናል" (ዕብ. 12:10) እንደሚል አምላካችን እንደ መልካም አባት የሚቀጣ ነው። ሲቀጣን አላማው ከቅድስናው እንድንካፈል ነው እንጂ ለመጉዳት አይደለም። የእግዚአብሔር ቅጣት ለጊዜው ሊያሳምም ቢችልም አላማው ግን እኛን ለማረቅና ለማቅናት እንጂ ለመስበር አይደለም። ስለዚህ የእግዚአብሔር ምርኩዝ አይጎዳንም ነገር ግን ያርመናል። መረን እንዳንወጣ ያደርገናል። ስለዚህ በበትሩ ከጠላት፤ በምርኩዙ ደግሞ ከራሳችን እንጠበቃለን።

ወገኖቼ፡- እረኛችን አስተማማኝ ጠባቂ ነው። ቃሉ "እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋምም" (መዝ. 121:4) እንዲሚል እርሱ ስለማይተኛ እኛ ተኝተን እናድራለን። እረኛችን ለራሳችንም አሳልፎ አይተወንም። ስለሆነም እንደ ዳዊት "በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ" ያጸናኑኛል እያልን እንዘምራለን። ስሙ የተመሰገነ ይሁን። አሜን!